# በሥራ ላይ የተመሰረተ ትምህርት - እንተርንሽፕ

የሥራ ላይ ስልጠናዎች /ልምምዶች ለ12ተኛ ክፍል ተማሪዎች ከዲስትሪክቱ በአንዱ የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት ጎዳናዎች ውስጥ ያለዉን እና ለወደፍት የሚፈልጉትን መስክ ለማሰስ እና የመለመመድ እድሎች ናቸው።

- ልምምዶች ለተማሪዎች የሚከፈሉ ወይም የማይከፈሉ እድሎች ልሆኑ ይችላሉ።
- በአብዛኛው የአንድ ሴሚስተር ጊዜ ወይንም ግን ረዘም ያለ ሊሆን ይችላል።
- ተለማማጆች ሳምንታዊ ማጠቃለያዎችን፣ የሰዓት ምዝግቦችን እና የመጨረሻውን ፕሮጀክት ያጠናቅቃሉ
- ለአማራጭ ኮርሶች 1.0 ክሬዲት እና የፍዳል ዉጤትንም ይቀበሉ
- በእንተርንሽፕ ሴሚናር ላይ ተሳትፎ

**መስፈርቶች፡**

- በ11ኛ ክፍል በስፕሪንግ ወቅት ማመልከት.
- ከ12ተኛ ክፍል ሠመር ወቅት በፊት ወይም በ12ተኛ ክፍል የመጀመሪያው ሴሚስተር ልምምድ ያጠናቅቁ
- ከተለማመዱ ልምምዶች ጋር የሚስማማ ተዛማጅ የCTE ኮርስ ስራ ቢያንስ 1 ሴሚስተር መመዝገብ ወይም ማጠናቀቅ አለበት።
- በመለማመጃ ቦታ ላይ ቢያንስ 100 ሰዓታት ማሳለፍ
- ወደ ኢንተርንሽፕ ቦታ እና ከቦታው የትራንስፖርት አገልግሎት የማቅረብ ኅላፍነት አለበት።
- ለመመረቅ በትክክለኛው ጎዳና ላይ መሆን
- የሠመር ተለማማጆች ለ CCSD የበጋ ትምህርት ቤት መመዝገብ እና ክፍያዎችን መክፈል አለባቸው (የነፃ ትምህርት ዕድል ሊኖር ይችላል) የሠመር ትምህርት ክፍያ መክፈል ካልቻላችሁ ለበለጠ መረጃ እባክዎን ኮኒ ኩክን (Connie Cook) ያነጋግሩ ccook8@cherrycreekschools.org

**እንዴት ማመልከት እንደሚቻል፡-**

1. የ CCSD የስራ ቦርድ ለቀጣዩ አመት ያሉትን የሥራ ላይ ልምምዶች ክፍት ቦታዎችን በስፕሪንግ ሴሚስተር ይከፈታል። የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በሙያቸው እና በቴክኒካል ትምህርት ኮርስ ስራቸው መሰረት ለ12ተኛ ክፍል ዓመታቸው ብቁ የሆኑትን ልምምዶች ማየት ይችላሉ።

2. ተማሪዎች ላሉ ልምምዶች ያመልክታሉ እና በተለማማጅ ኢንዱስትሪ አጋር ይመረጣሉ
3. ተማሪዎች ከተመረጡ በኋላ ልምምዳቸውን በሚሰሩበት ሴሚስተር ውስጥ በ በእንተርንሽፕ ሴምስተር ውስጥ ይመዘገባሉ.
4. የሚከፈልበት እንተርንሽፕ ከሆነ፣ ተማሪው የሚከፈለው እንተርንሽፕ በሚያቀርበው ቀጣሪው በተገለፀው መሰረት የመቅጠር እና ለስራ ብቁነት መስፈርቶችን ማሟላት አለበት።

- **አብዛኛዎቹ የስልጠና ስራዎች ከዲስትሪክቱ የCTE የሙያ እና የቴክንክ መስመሮች ጋር የተጣጣሙ ናቸው። የሙያ መንገዶቹ ምንድርናቸው?**
- የንግድ አስተዳደር
- የሚዲያ ጥበባት
- እንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ
- ምህንድስና እና ቴክኖሎጂ
- የጤና ሳይንስ

- ህግ፣ የህዝብ ደህንነት፣ እርማቶች እና ደህንነት
- መስተንግዶ እና ቱሪዝም
- ሰብአዊ አገልግሎቶች
- አርክቴክቸር እና ግንባታ
- ማኑፋክቼሪንግ
- መጓጓዣ, ስርጭት እና ሎጂስቲክስ
- የውጪ መዝናኛ አመራር

*የሥራ ላይ ልምምዶች በእያንዳንዱ በላይ በተጠቀሱት መስመሮች ላይ ላይገኙ ይችላሉ። ልምምዶች ከአመት ወደ አመት ይቀየራሉ.*

በእያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁሉም ከላይ የተጠቀሱት ኮርሶች አይሰጡም። Contact your school counselor or refer to the school's course guide for more information. ለበለጠ መረጃ የትምህርት ቤቱን የትምህርት አማካሪን ያነጋግሩ ወይም የትምህርት ቤቱን የኮርስ መመሪያ ይመልከቱ።

**ለበለጠ መረጃ**

የተማሪውን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማካሪ ያነጋግሩ
በስራ ላይ የተመሰረተ የመማሪያ ቡድንን ያነጋግሩ
(Tara Bell,)የድህረ ሁለተኛ ደረጃ የስራ ኃይል አስተዳዳሪ, tbell18@cherrycreekschools.org
(Ashlin Montgomery)የስልጠናዎች አጋር amontgomery12@cherrycreekschools.org
Margaret Krob, (ረዳት), mkrob@cherrycreekschools.org